# አህጉራዊ አሻራችን በ50ኛው አፍሪካዊ ልደት ሲታወስ

**ማህደር ዋሲሁን**

05/26/13

**እንደ መግቢያ**

ዛሬ እንደዘበት የምንሰማው የአፍሪካ አንድነትና ህብረት እንቅስቃሴ መቀንቀን የጀመረው በርካታ የአህጉሪቱ ሀገራት ነፃ ከመውጣታቸው በፊት ነው። እንቅስቃሴው በባሪያ ፍንገላ ወቅት ከእናት አህጉራቸውን በመሰደድ ወደ ውጭ /አሜሪካ፣ ካሪቢያንና ደቡብ አሜሪካ/ በሄዱና በሂደት ለትምህርት ወደ አውሮፓ ባቀኑ አፍሪካውያን ትብብር አማካኝነት የአፍሪካዊነት ህብረት እንቅስቃሴ (pan African movement) የተፈጠረ ለመሆኑ ድርሳናት ያመለክታሉ። ይህ ዕውነታም አፍሪካ እንደ አህጉር የአንድነት/የህብረት ድርጅቷን ከመሰረተች 50 ዓመታትን ብታስቆጥርም ቅሉ፤ የአንድነቱም ይሁን የህብረቱ እንቅስቃሴ ሽል ከተጸነሰ ከመቶ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ መሆኑን ያስረዳል።

ከአስከፊው የቅኝ አገዛዝ መንጋጋ ለመጀመሪያ ጊዜ የተላቀቀችው ምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ጋና ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ሲላቀቁ፤ እንቅስቃሴው በየትም አካባቢ የሚገኙ ጥቁሮች ብቻ መሆኑ ቀርቶ በአፍሪካ የሚኖሩ ህዝቦች ከፍ ሲልም የአህጉሪቱ ሀገራትና መንግስታት ጭምር ሊሆን ችሏል። ታዲያ የአፍሪካ አንድነትና ህብረት ጥያቄ የሀገራቱና የመንግስታቱ ዋነኛ ጥያቄ ሆኖ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሲሆን፤ ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች በይፋ መውጣት ጀመሩ።

አንደኛውና ግንባር ቀደሙ ከቅኝ ግዛት ነፃ ያልወጡ የአፍሪካ ሀገራት ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ሀገራቱ በጋራ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አፍሪካ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖራት ተባብሮ የመስራት መርህን ያነገበ ነበር። ከዚህ ጎን ለጎንም የወቅቱ የጋና ፕሬዚዳት ክዋሜ ንክሩማ የሚመራው ቡድን “በአፍሪካ ደረጃ አንድ የጋራ መንግስትና ኢኮኖሚ መፍጠር አለብን፣ ይህንንም አሁኑኑ ማከናወን ይኖርብናል” የሚል አቋም ሲያራምዱ፣ ዓፄ ኃይለ ስላሴ የሚገኙበት የአብዛኛው ሀገራት ደግሞ አስተሳሰቡ ዕውን ሊሆን እንደማይችል በመግለጽ፣ “ከቅኝ አገዛዝ የወረስነውን ድንበር ይዘን እንደ ነፃ ሀገሮች በመደራጀት በአፍሪካዊነታችንና በነፃ መንግስታት መካከል በሚኖር ትብብር ነው መመስረት የምንችለው” የሚል አቋምን አራመዱ። የኋላ ኋላ ግን ነገሩ መፅሐፉ “ብዙሃን ይመውዑ” / ብዙሃን ያሸንፋሉ/ እንዲለው ሆኖ ነው መሰል፤ ውህዳኑ የእነ ንኩርማ ቡድን በብዙሃኑ ሃሳብ

በመዋጡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU) እ.ኤ.አ. በወርሃ ግንቦት1963 ዓ.ም. ነፃ የአፍሪካ ሀገሮች የመሰረቱት በይነ-መንግስታዊ ድርጅት (Inter Governmental Organization) በመሆን አዲስ አበባ ላይ ተመሰረተ። የዛሬው የ50 ዓመት ጎልማሳ የአፍሪካውያን አንድነት ቋጠሮ።

ድርጅቱ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ሁለት ሃሳቦችን አንግቦ የተጣለበትን ኃላፊነት ለ39 ዓመታት ያህል መወጣቱ ስለታመነበት፤ የዛሬ 11 ዓመት ገደማ በደቡብ አፍሪካ ደርባን በተካሄደ የድርጅቱ ጉባኤ በይፋ ወደ አፍሪካ ህብረትነት (AU) እንዲተካ ተደረገ።… ታዲያ ይህን ያህል ግንዛቤ እንደ መግቢያ ስለ ህብረቱ አመጣጥ ከያዝን ዘንዳ፤ እስቲ አሁን ደግሞ የጉዳያችን ማጠንጠኛ ስለሆነውና ሀገራችን በዚህ የ50 ዓመት የአንድነቱ/የህብረቱ ጉዞ ውስጥ ስላበረከተችው አስተዋፅኦ እናውጋ።

## አፍሪካዊ አሻራችን

ሀገራችን ከተወለደ የግማሽ ምዕተ- ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረውን አህጉራዊ ድርጅት ከማዋለድ ጀምሮ በማሳደግና ወደ ኅብረትነት እንዲቀየር በማድረግ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ድርሻዋን ተወጥታለች። ሀገራችን እንደ መስራችና እንደ ዋና መቀመጫነቷም የትኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ይሁን የቱም በአፍሪካዊ ወንድማማችነትና መንፈስ ተቀብሎ በማስተናገድ፣ ጭቆናና በደልን፣ ግፍና ብዝበዛን በመቃወም አቅሟ የፈቀደውን ሁሉ አድርጋለች። አለመግባባትና ግጭቶች ሲከሰቱም በማብረድ ረገድ ተሳትፎዋ ቀላል አልነበረም። በአህጉሪቱ የሚፈጠር አለመረጋጋትን በመረጋጋት በመተካት፣ የተጎዱትን በማቋቋምና የተቸገሩትን በመርዳት የማይናወጥ አቋሟን ስታንጸባርቅ ኖራለች። ኢትዮጵያ አህጉሪቱን ከቅኝ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ በማውጣትና አፍሪካውያን ነጻነታቸውንና ክብራቸውን ለመመለስ እንዲሁም አፍሪካን ወደ ኢኮኖሚ ዕድገት ለመምራት በተደረገው ትግል የማይነጥፍ አስተዋጽኦ ስታደርግም ቆይታለች።

ከድርጅቱ ምስረታ በፊት አፍሪካን ለሁለት ከፍሏት በነበረው በክዋሜ ንኩርማና በብዘሁኑ ቡድኖች መካከል የነበረው የአካሄድና የአስተሳሰብ ልዩነት እንዲፈታ በማድረግ ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች። ሀገራችን ወራሪውን የጣሊያን ኃይል ታግላ ነጻነቷን በማስመለስ ያስመዘገበችው ድል በአህጉሪቱ ለነጻነት ሲደረግ የነበረውን ትግል በማቀጣጠል በርካታ ሀገሮች ነጻነታቸውን እንዲጎናጸፉ አድርጓል። እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ አፍሪካውያን በቅኝ አገዛዝ ሲሰቃዩ በዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት እየቀረበች በሕግ ትሟገትላቸውና ትከራከርላቸው የነበረችውም ሀገራችን ናት። በቅኝ አገዛዝና በአፓርታይድ ሥርዓት ሲሰቃዩ የነበሩ አፍሪካውያን የሞራል፣ የዲፕሎማሲና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሚናዋንም በሚገባ ተወጥታለች።

በንጉሱ ዘመን ሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ጥሪ በመቀበል የሰላም አስከባሪ ሃይሏን ለሁለት ዓመታት በኮሪያ ልሳነ ምድር አዝምታለች። በአሁኗ ኮንጎ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ የነበረውን ችግር ለመፍታትም የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል እ.ኤ.አ. ከ1960 እስከ 1964 በነበረው ጊዜ ውስጥ ግዳጇን ሥነ-ምግባር በተሞላበትና ሁኔታ የተሳካ ሥራ አከናውኗል። ለደቡብ አፍሪካ፣ ለናሚቢያና ለዚምባቡዌ የነጻነት ትግል ወታደራዊ ስልጠና በመስጠት ያደረገችው አስተዋጽኦም በታሪክ ሲወሳ የሚኖር ነው።

ከደርግ ግብዓተ-መሬት በኋላ ሰላም መርሁ የሆነው መንግስታችን አፍሪካዊ አስተዋጽኦውንና ሃላፊነቱን ከምንጊዜውም በላቀ ሁኔታ ተወጥቷል፤ እየተወጣም ነው። በዚህ መሰረትም በሩዋንዳ እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ በተከሰተውና የዓለምን ሕዝብ ባስደነገጠው የዘር ማጥፋት እንቅስቃሴ ሠላም እንዲያስከብሩ ከተደረጉት ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ እንድትሆን አስችሏል። እ.ኤ.አ. አዲሱ ሚሌኒየም ሲጀመር በቡሩንዲ ሁቱና ቱትሲ የተባሉ ጎሳዎቿ ግጭት ውስጥ ነበሩ። ዘር ለይቶ የተፈጠረውን ዘግናኝ ድርጊት ለማስቆም በአፋጣኝ ሠላም አስከባሪ ኃይላቸውን እንዲልኩ ከተደረጉት ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ ቀዳሚዋ ናት። በዚህም ታሪካዊ አስተዋጽኦዋን አበርክታለች። በላይቤሪያም እንዲሁ። ላይቤሪያ ባለፈው የአውሮፓውያን አስርት መጨረሻ ዓመታት ላይ በከፍተኛ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ነበረች። ሀገሪቱን ወደ ሠላምና መረጋጋት ጎዳና ለመመለስ በተደረገው ሂደት የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል ተሳትፎ ወደር አልነበረውም። በሀገሪቱ ሠላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በማድረግም ሚናውን ተጫውቷል።

በሱዳን ዳርፉር ግዛት ከሌሎች ሀገሮች ጋር በመሆን ባሰማራችው ሠላም አስከባሪ ሃይልም የእርስ በርስ ግጭት እንዳይከሰት በማድረግ ላይ መሆኗም ይታወቃል። ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በይገባኛል በሚከራከሩበት የአብዬ ግዛት ከዓለም ብቻውን የተሰማራ ሠላም አስከባሪ ኃይል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ሥር በማሰማራት በዓለም- አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቷን ያሳደገ ተግባር እያከናወነች ነው። ሀገራችን በሁለቱም ሀገሮች መንግሥታትና ሕዝቦች ያላት አክብሮትም ከፍተኛ ነው። ሀገራችን በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ሠላም፣ ጸጥታና መረጋጋት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ባለችው ሚና በሶማሊያ የነበረውን መንግሥት- አልባነትና አክራሪነት በመታገልም ውጤታማ መሆን ችላለች። እርግጥ ሠላማቸው የተረጋገጠ፣ በኢኮኖሚያቸው የበለጸገና ዴሞክራሲ ያበበባቸው ጎረቤቶች የጋራ ጥቅም መሠረት መሆናቸው የማይታበይ ቢሆንም፤ ሀገራችን ከዚህ ባለፈ ለጎረቤቶቿ ህዝቦች ሰላም ያለማሰለስ በመሥራት ላይ ትገኛለች። ባለፉት 50 ዓመታት በሞሮኮና በአልጄሪያ፣ ናይጄሪያ ውስጥ የቢያፍራ የመገንጠል እንቅስቃሴን እንዲሁም በሱዳን የኛኛ እንቅስቃሴ ከማዕከላዊ መንግሥታት ጋር የነበራቸውን ግጭት በመፍታት ታሪካዊ አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ሀገራችን በኢኮኖሚው መስክ ያላት አህጉራዊ ትብብር ኮሜሳ በሚሰኘው በምሥራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ የተጠናከረ ውህደት ለመፍጠር ያላት ሚናም ከፍተኛ ነው። በመሠረተ-ልማት ግን ባታ መስክ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለመሳብም ጥረት ታደርጋለች። የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግም በመሥራት ላይ ነች። ከጅቡቲ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ጋር የመንገድ ግንኙነት በመፍጠር ለጋራ ጥቅም በመትጋት ላይ ትገኛለች። ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኝ የባቡር መሥመር ግንባታው በመካሄድ ላይ ሲሆን፤ ከኬንያ ጋር የሚያገናኘው መሥመር በቅርቡ ይጀመራል ተብሎ ይጠበቃል። ለጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ተጠቃሚ እንድትሆን ከማድረጓም በላይ፤ ኬንያንም በተመሳሳይ ሁኔታ እንድትጠቀም እንቅስቃሴ እያደረገች መሆኗን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃዎች ያመለክታሉ።

የአባይ ውኃ አጠቃቀም ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መጠቀም አስፈላጊነቱን አምናም እየሰራች ነው። የናይል የላይኛው ተፋሰስ ሀገሮች የጋራ ማዕቀፍ ፊርማ ወደ ማጽደቅ ሂደት በመግባት ላይ ነች። ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በመገንባት 6ሺህ ሜጋ ዋት በማመንጨት ዓላማዋ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ጎረቤት ሀገሮችንም መጥቀም ነውና። በአህጉሪቱ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲን ለማስፈን የተያዘውን ጥረትም በአፍሪካ እርስ በርስ መገማገሚያ ስልትም እየተገበረችው ነው። ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ የተገነባበትን 2ሺህ ስኩዬር ሜትር መሬት መስጠቷም የአሻራችን አንድ ክፍል ነው። ባለፈው ዓመት የተመረቀው አዲሱ የአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ቤት ግንባታ መሬት በነጻ በመስጠትና የቻይናን መንግሥት በማግባባት ያደረገችው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም። በአዲስ አበባ ኤምባሲያቸውን ለከፈቱ የአፍሪካ ሀገሮች ሕንጻ ግንባታም ቦታ በመስጠትም ድጋፏን ሰጥታለች። ሀገሪቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን/የአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ቤትን በአዲስ አበባ ከተማ በማስተናገዷ ከሁሉም በፊት በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻሻል አድርጋለች። ከዚህ በተጨማሪም ከተማዋ የዓለም- አቀፍ ዲፕሎማሲ መናኸሪያ እንድትሆን አድርጋለች። በዚህ ረገድ የሚወዳደሯት ኒውዮርክ፣ ጄኔቫና ብራስልስን የመሳሰሉ ከተሞች ብቻ ናቸው። በከተማዋ የሚደረጉት ጉባዔዎች፣ ስብሰባዎችና ዐውደ ጥናቶችና ሌሎችም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስገኘትም ያስገኙት ዋጋ ከፍ ብሎ ይታያል።

አዎ! ሀገራችን ከላይ በተገለፀው መልኩ ከፍተኛ ድርሻ ማበርከቷ ሲወሳ መሪዎቿም አብረው መነሳታቸው አይቀሬ ነው። እንደሚታወሰው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውልደቱ በአፄ ኃይለሥላሴ የስልጣን ዘመን ነበር። መንግስቱ ኃይለማሪያም በሚመራው አምባገነናዊው የደርግ ስርአት ወቅትም ድርጅቱ የራሱን የታሪክ ሂደት አሳልፏል። ታዲያ በእነዚህ የመንግስት ስርአቶች የነበሩት እውነታዎች በሚታወሱበት ወቅት ያለፉት ገዢ መደቦች ለሀገራቸውና ለህዝባቸው

የማይመቹ፣ በጨቋኝነታቸውና በበዳይነታቸው ይታወቁ የነበሩ ቢሆኑም፤ በአፍሪካ ጉዳይ ግን ጠንካራ አቋም እንደነበራቸው አይዘነጋም።

የአፍሪካ ህብረት ምሥረታ የመሪዎች ጉባዔ ውይይት በቶጎ ርዕሰ ከተማ ሎሜ ላይ በተካሄደበት ወቅት፤ የሴኔጋል ፕሬዚዳንት የነበሩት አብዱላሂ ዋዴ 'የህብረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ ይሆናል' የሚለውን አንቀጽ እንደማይቀበሉት አስታውቀው ነበር፡፡ ታዲያ በወቅቱ ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ ባቀረቡት የማሳመኛ ሃሳብ፤"...እረ ለመሆኑ ማነው ማንዴላን ያሰለጠነው?- ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው፡፡ አድሃሪው ኃይለ ሥላሴ ናቸው አብዮታዊውን ማንዴላን ያሰለጠኑት፡፡ ...ማነው ሮበርት ሙጋቤ ከሮዴሽያ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት በሚፋለምበት ወቅት የረዳው? -መንግሥቱ ነው፡፡ መንግሥቱ ኃይለማርያም በሀገር ውስጥ አምባገነንና ጨፍጫፊ ነው፡፡ ነገር ግን በአፍሪካ ጉዳይ  ልክ እንደ ኃይለ ሥላሴ አቋሙ ጠንካራ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ መሪዎች ቢለዋወጡም፤ በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ግን አቋማቸው አንድ ነው፡፡ የአዲሱ አፍሪካ ህብረት መቀመጫ አዲስ አበባ መሆን የለበትም፣ ለእኔ ይገባኛል የሚል ካለ እውነቱን ፍርጥርጥ አድርገን ልንነጋገርበት እንችላለን..." በሚል ያቀረቡት ለዚህ አባባሌ እማኝ የሚሆን ይመስለኛል።

የደርግ ሥርዓት ውድቀትን ተከትሎ ሀገራችን በዚህ አህጉር- አቀፍ ተቋም ውስጥ ያላት ሚና ወደ ላቀ ደረጃ የተሸጋገረበት ታሪካዊ ምዕራፍ ሊከፈት በቅቷል፡፡ በዚህም ውስጥ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ስምና ተግባር በግንባር ቀደምትነት የሚነሳ ነው፡፡ ታላቁ መሪያችን በሀገር ውስጥ ለተቀጣጠለው ድህነትን የመዋጋት ዘመቻ የነበራቸውን ውጤታማ የመሪነት ሚና፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለህብረ ብሄራዊ የፌዴራሊዝም ሥርዓቱ የነበራቸውን  አስተዋፅኦ፣ በሀገር ውስጥ የሚደረጉ የሽብርተኝነትን በመከላከልና በመታገል ረገድ የነበራቸውን ጽኑ አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለአፍሪካ አህጉር ሰላምና ብልጽግና ቀን ከሌት ሲታገሉ የኖሩ፤ ለብዙ አፍሪካውያን ዘንድ የሰላም፣ የመቻቻል፣ የእኩልነትና የብልፅግና ናፋቂነት ቀና መንፈስ ማስታጠቅ የቻሉ ባለ ራዕይ መሪ ናቸው።

አዎ! አቶ መለስ የአፍሪካ ህብረት ጠንካራ አህጉራዊ ድርጅት እንዲሆን ወደር የሌለው ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል። በህብረቱ ውስጥ በሚነሱ ወሳኝ አጀንዳዎች ዙሪያ አባል ሀገራት በሰጥቶ መቀበል መርህ መሰረት የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችለዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች አጋሮቻቸው ጋር በመሆን በፈጠሩት ለአፍሪካ ልማት አዲስ አጋርነት የተጫወቱት ሚና እንዲሁም የአፍሪካ ድምፅ በዓለም መድረኮች እንዲሰማና አህጉሪቱ በዓለም - አቀፍ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የሠላም እና የፀጥታ እንቅስቃሴዎች ተገቢውን ትኩረት እንድታገኝ አድርገዋል።

ዓለማችንን በከፍተኛ ደረጃ እየተፈታተነ የሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥና ጫናውን በፍጥነት ከመግታት አኳያ ታላቁ መሪያችን ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መስመር

እንድትመራ ቀመሩን ከመንደፋቸው ባሻገር፣ መላው የአፍሪካና የዓለም ሀገራት በዚህ መስመር እንዲጓዝ ያመላከቱ ታላቅና ጀግና መሪ ሲሆኑ፣ ለዓለም ሙቀት መጨመር የአፍሪካ ሀገራት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ አነስተኛ መሆኑን በማስታወቅ  የጉዳት ካሳ እንዲያገኙ የተጀመረውን እንቅስቃሴ ከመጠንሰስ እስከ መምራት የደረሱ ቆራጥና ብልህ መሪ ናቸው፡፡ አቶ መለስ የህብረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ ሆኖ እንዲቀጥል በፅኑ የታገሉና ለስኬት የበቁም ናቸው፡፡ በዚህም አንዳንድ ለሀገራችን በጎ አመለካከት ያልነበራቸው ሀገራት አዲሱ የአፍሪካ ህብረት ጽሕፈት ቤት ከአዲስ አበባ እንዲነሳ የነበራቸው ሃሳብ ከምኞት እንዳይዘል አድርገዋል፡፡

እርግጥ ላለፉት 40 እና 50 ዓመታት ሰብዓዊ ጥፋት ያስከተሉ ጦርነቶች የተካሄዱበትን የምስራቅ አፍሪካን ቀጣና ማረጋጋት ቀላል ባይሆንም፣ ታላቁ መሪያችን ግን ለሠላምና መረጋጋት ጠንቅ የሆኑ አካሄዶችን በሣል በሆነና ብቃት ባለው አካሄድ እየተመሩ ያጋጥሙ የነበሩ ፈተናዎችን በድል ተወጥተዋል፡፡ አሸባሪነትና አክራሪነት በቀጣናው እንዳያቆጠቁጥና ምሥራቅ አፍሪካ ከጽንፈኞች ሥጋት ነፃ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረትም አድርገዋል፡፡ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት መንግሥት አልባ በነበረችው ሶማሊያ የመሸገው “እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት” በወቅቱ በሀገራችን ላይ ደቅኖት የነበረውን ግልጽና ድርስ አደጋ ብሎም በምሥራቅ አፍሪካ ሰማይ ላይ እንዲያንዣብብ ያደረገውን የጦርነት ደመና ብስለት በተሞላው ዘዴ አስወግደዋል፡፡

በወቅቱ የኢጋድ አባል ሀገራትንና አፍሪካ ህብረትን ከጎናቸው በማሰለፍ የሶማሊያ አክራሪ ፅንፈኞች አከርካሪያቸው እንዲሰበር ለማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህም በአንድ መልኩ እንደ መንግሥት በአስተማማኝ ዲፕሎማሲ የሚመሩ መሆናቸውን ያረጋገጡ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሠራዊታችን ማንኛውንም ግዳጅ በብቃት መፈጸም የሚችል ቁመና እንዳለው ለዓለም - አቀፉ ማኅበረሰብ በማሳወቅ አስተማማኝ ወታደራዊ ዲፕሎማሲ የገነቡ ታላቅ መሪ ናቸው፡፡ ራሱን “አል-ሸባብ” እያለ የሚጠራው የሶማሊያ ሽብርተኞች ቡድን በቀጣናው ሠላምን ለማናጋት ያደረገውን አፍራሽ እንቅስቃሴ ፈጥነው በመረዳትም ከምሥራቅ አፍሪካና የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ጋር በመሆን ወሣኝ ድርሻን አበርክተዋል፡፡ በዚህ ረገድ በኢጋድና በአፍሪካ ህብረት ውስጥ ባከናወኑት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ሌሎች ሀገራትም ሠራዊታቸውን ወደ ሶማሊያ እንዲልኩ የማግባባት ተግባራትን ፈጽመዋል፡፡

ከዚህ በዘለለም፣ በዚያች ሀገር ውስጥ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍንና ቋሚ መንግሥት እንዲፈጠር ሌት ተቀን ሲሰሩ ነበር፡፡ በዚህም ዛሬ ሶማሊያውያን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲያካሂዱ ጥርጊያ መንገድ በማመቻቸት ወደር የሌለው ሚና ተጫውተዋል፡፡ከሁሉም ጎረቤት ሀገሮች ጋር በሠላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለመፍጠር ደፋ ቀና ይሉ የነበሩት እኚህ ታላቅ የአፍሪካ ልጅ፣ ለየትኛውም ወገን የማይወግን የዲፕሎማሲ አካሄዳቸውን

በመጠቀም ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ችግራቸውን በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ አስችለዋል፡፡፡ ባላቸው ለማንም ያልወገነ አቋም በሁለቱም ሀገሮች እኩል ተቀባይነት የነበራቸው አቶ መለስ፤ በመንግሥታቱ ድርጅት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሁለቱም ሱዳኖች የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት እንዲመርጡ ምቹ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዲፕሎማሲን መፍጠር የቻሉ መሪ ናቸው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም። በሱዳን - ዳርፉር የተፈጠረውን ቀውስ ለማርገብ የሱዳን መንግሥትና የደቡብ ሱዳን ነፃነት ንቅናቄ "ሁሉን አቀፍ የሠላም ስምምነት" (Comprehensive Peace Agreement 'CPA') እየተባለ የሚጠራውን ሰነድ እንዲፈራረሙ ብርቱ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አድርገዋል፡፡ ከዚህ ባሻገርም፤ ለሠላም ካላቸው ፅኑ ፍላጎት በመነሳት የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ በዳርፉር (UNAMID) ጥላ ስር የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በሠላም አስከባሪነት እንዲሰማራ በማድረግ በዚያች ሀገር መረጋጋት እንዲፈጠር ጥረዋል፡ ፡ በእነዚህ ቀጣናዊ ተግባሮቻቸው በአፍሪካ ሕዝቦች ዘንድ ታላቅ አክብሮትን ማግኘት የቻሉ አርቆ አስተዋይ መሪ ናቸው፡፡

የባለ ራዕዩ መለስ ሠላምን የተመረኮዙ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ብቻ ያተኮሩ አይደሉም፡፡ ከዚህም አልፎ የመላው አፍሪካ ድምፅ በመሆን ዓለም - አቀፍ ተቀባይነትን ወደ ማግኘትም የተሸጋገሩ ናቸው፡፡ ታላቁ መሪያችን አፍሪካውያን በመሠረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እንዲወስዱ በዓለም- አቀፍ መድረኮች ላይ የአህጉሪቱ ቃል አቀባይ ሆነው ውጤት ማስገኘት የቻሉ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በተለይም በየዓመቱ በአማካይ በሁለት ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይጨምራል ተብሎ በሚጠበቀው ዓለም - አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ "አፍሪካ ዋነኛዋ ተጎጂ ናት" በማለት የምዕራቡ ዓለም በኢንዱስትሪ ሣቢያ ለፈጠረው የካርቦን ልቀት ለአህጉሪቱ ካሣ እንዲከፍል በመጠየቅ ከአፍሪካ ሕዝቦች ባሻገር፤ ከራሳቸው ካደጉት ሀገራት ጭምር አንቱታን ለማትረፍ ችለዋል። አቶ መለስ በኮፐንሃገን፣ በሜክሲኮ ወዘተ. በተካሄዱ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔዎች፤ አፍሪካ በለውጡ ይበልጥ ተጎጂ የሆነችው የአየር ንብረቷ ተጋላጭ፣ ለውጡን ለመቋቋም ያላት ገንዘብና ቴክኖሎጂ ውስን እንዲሁም አህጉሪቱ ዕድገቷን በአዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂ ዙሪያ ለመገንባት ያላት አቅም ከበለጸጉት ሀገሮች በአያሌው ያነሰ መሆኑን በማስረዳት በብርቱው የተከራከሩና አበረታች ውጤት ያመጡ ናቸው፡፡

በዚህ ተግባራቸውም የአፍሪካ አለኝታና መከታ መሆናቸውን በአደባባይ አስመስክረዋል፡፡ ይህን የዲፕሎማሲ እምቅ አቅማቸውንና ክሂላቸውን የተገነዘበው ዓለም - አቀፉ ማኅበረሰብ በተለይም የበለፀጉት ሀገራት በቡድን ስምንት እና 20 ስብሰባዎች ላይ ከሚገኙት በጣት የሚቆጠሩ የአፍሪካ መሪዎች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጋበዙ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ እናም ቀደም ሲል በረሃብና በጦርነት የምትታወቀውን ሀገራችንን ስም በአዲስ የዲፕሎማሲ መንገድ አራማጅነት እንዲቀየር ለማድረግ የቻሉ የሀገራችንና የአፍሪካ ባለውለታ ናቸው፡፡ እንግዲህ ባለፉት 50

የአፍሪካ ጉዞ ሀገራችን ያከናወነቻቸው ተግባራት በጥቂቱ ተጨልፈው ሲታወሱ ይህን ይመስላል። እነዚህ ሃቆች በደምሳሳውም ቢሆን የሚያሳዩን ሃቅ ቢኖር የሀገራችን አፍሪካዊ አሻራነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ነው።

## እንደ ማጠቃለያ

በአሁኑ ወቅት የሀገራችን አሻራ ጎልቶ የሚታይበት አፍሪካዊ ተቋም የተመሰረተበት 50ኛ ዓመት የወርቅ እዮቤልዮ በዓልን በማክበር ላይ እንገኛለን። ይህ በዓል ለአፍሪካ ህብረትና አንድነት መሰረት የጣሉትን የድርጅቱ መስራች አባቶችና የፓን አፍሪካ እንቅስቃሴ መሪዎችን ለመዘከር ልዩ አጋጣሚ ይፈጥራል። በዓሉ አህጉሪቱ ባለፉት አምስት አስርት ዓመታት ያሳለፈችውን ጉዞ እንዲሁም አባል ሀገራት በአፍሪካ ሠላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማትና ዕድገት እንዲረጋገጥ ያላቸውን ተስፋና ፅኑ ፍላጎት የሚገልፁበትና የአፍሪካ ህዳሴ እውን እንዲሆን ቁርጠኝነታቸውን ዳግም የሚያረጋግጡበትም ይሆናል።

ታዲያ ክብረ-በዓሉ ሀገራችን ውስጥ መከበሩ የተለየ ትርጉም ያለው መሆኑን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ መገንዘብ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሀገራችን ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ለድርጅቱ ያበረከተቻቸው አስተዋፅኦዎች ይበልጥ እውቅና እንዲያገኙና ለዚህም ተገቢውን ክብር እንዲሰጣት ከማስቻል ባሻገር፤ የሀገራችንን መልካም ገፅታ ለመገንባት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ማንም በዓሉን የተከታተለ ሰው አፍሪካዊ አሻራችን ሲታወስ ከመደመሙም በላይ፤ ኢትዮጵያ አፍሪካ፣ አፍሪካም ኢትዮጵያ መሆኗን ይገነዘባል– ላለፉት አምስት አስርታት እኛና አህጉሪቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች እንደነበርን። ቸር እንሰንብት።